# የጉዳዩ ባለቤት ከሆኑ ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ

## አጭር መግለጫ

የስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች ከሁሉም የህብረተሰቡ ክፍል አባሎች ጋር ጠንካራና ዘላቂ የሆነ ግንኙነት እንዲኖር ለማድርግ ትልቅ ጥረት ያደርጋል።ከመላው አገር ውስጥ የስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤት የበለጠ ትምህርትቤት እንዲሆን ለማድረግ ከህብረሰተቡ ጋር ጥሩ ግንኙነት በመፍጠርና ተባብረን ለመስራት እንፈልጋለን።

## ዋና አስፈላጊ ነገሮች

የጉዳዩ ባለቤት የሆነው ህብረተሰብ እንዴት ማሳተፍ እንደሚቻል አንድ ፕላን በመጪው ወር ውስጥ ፕላን እንዲነደፍ ይደረጋል። የሚነደፈው ፕላን ከተጠናቀቀ በሃላ ሪፖርቱ ለት/ቤቱ ቦርድ እንዲቀርብ ይደረጋል።

አሰራራችንን ለማሻሻልና እድገት ለማምጣት እንድንችል ዘንድ ከሁሉም የህብረተሰቡ አባሎች አስፈላጊውን ሃሳብና አስተያየቶች ለማግኘት እንፈልጋለን።

**ወላጆች በይበልጥ እንዲሳተፉ ማድረግ** – የወላጆችና ትምህርትቤት ወዳጅነት አማካሪ ኮሚቴ እንደ ጥሩ አርአያ ሊጠቀስ ይቻላል።ወላጆች በክፍል፣ በትምህርትቤት፣ በክልል ደረጃ በማናቸው ጊዜ ተሳታፊ እንዲሆኑ እንፈልጋለን። ወላጆች ያላቸውን አስተያየቶች ለማወቅና ለመስማት እንፈልጋለን።

**ከኮሚዩኒቲው አባሎችና መሪዎች ጋር ጥሩ ግኑኝነት መፍጠር** – የኮሚዩኒቲው አባሎች ሁሉ ስለ የኛ እንቅስቃሴና እድገትና እንዲሁም ስለ ተማሪዎች ማናቸውም መረጃዎች ሁሉ ለማወቅ ይፈልጋሉ።ስለሆነም የምናካሂዳቸው ስራዎችና ስለምንወስናቸው ጠቃሚ ውሳኔዎች ሁሉ እንዲያውቁት ማድረግ አስፈላጊ ነው።የኮሚዩኒቲ አባሎች ምን መረጃዎች ለማወቅ እንደሚፈልጉን እንዲሁም እንዴት በምን መንገድ ለመሳተፍ እንደሚችሉ ለማወቅ እንፈልጋለን።

**የትምህርትቤቱ ሰራተኞች ዋና ተዋኒያን እንዲሆኑ ማድረግ** – የኛ አስተማሪዎች፣ ርእሰ መምህራንና ሌሎች ሰራተኞች ከክልሉ አስተዳደርና ከወላጆች ሁሉ በምናደርገው ግንኙነቶች ሁሉ ዋና መልእክተኞቻችን ናቸው።ከነሱ የምናገኛቸው ሃሳቦችና አስተያየቶች ሁሉ ጥራት ላላቸው ስራዎች ለመስራትና እንዲሁም ለምንወስናቸው ውሳኔዎች ሁሉ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።

**ከኮሚዩኒቲው አባሎች ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ** – ለተማሪዎቻችን፣ አስተማሪዎቻችን፣ ለትምህርትቤቶቻችንና ለአስተዳደሩ ክፍል የተለያዩ እርዳታና ድጋፍ የሚያደርጉልን የተለያዩ ወዳጆች አሉን።ስለሆነም ከእንደነዚህ የመሳሰሉትን ወዳጆች ሁሉ ያለንን ግኑኝነት እንዲጠነክር ማድረግ ወሳኝ ነው።

**ህዝቡ እምነት እንዲያድርበት ማድረግ** - የስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤት ክልል አስተዳደር ያለውን የወደፊት አላማ፣ ርእይና ፕላን ምን እንደሆነ ለህብረተሰቡ በየጊዜው ማስታወቅ አለበት።ስለ አሰራራችንና የወደፊት አላማ ምን እንደሆነ በግልጽ ከህብርተሰቡ ጋር በመነጋገር ያለንን ግንኙነት ጠንካራ ለማድረግ እንደሚቻል እንተማመናለን።

**የኢንቴርኔት ዌብ ሳይት ማሳደስ**– የስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች በይበልጥ ከህብረተሰቡ ጋር ለመተዋወቅና ማንነታችንን ለማስታወቅ እንዲሁም ያሉንን ጠቃሚ መረጃዎች በቀላሉ ለህብረተሰቡ እንዲዳረሱ ለማድረግ የኢንቴርኔት ዌብ ሳይት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።ስለሆነም ከኢንቴርኔት ዌብሳይታችን ምን አይነት መረጃዎች ማግኘት እንደምትፈልጉ ያላችሁን አስተያየት እንድትገልጹልን እንፈልጋለን።

## ለህብረተሰቡ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

- በይበልጥ ለማወቅ የምትፈልጉት ነገር ምንድነው?
- ግልጽ ያልሆነላችሁ ነገር ካለ?
- የጎደለ ነገር ካለ?
- ስለ አሰራራችን ያሉት መረጃዎች ሁሉ በምን መንገድ እንዲደርሳችሁ ትፈልጋላችሁ?